# ኢ.አአግ የተጋድሎ ታሪኩንና ፖሊሲውን በአውስትራሊያ ለኢትዮጵያውን አስተዋወቀ::

የኢትዮጵያ አርበኞች አንድነት ግንባር/ኢ.አአግ እሑድ እ.ኤ.አ ኦክቶበር 29 2006 ዓ.ም መድረክ ኢትዮጵያ በአውስትራሊያ በአዘጋጀው ሕዝባዊ የውይይት መድረክ ላይ በመገኘት የድርጅቱን አመሠራረት ታሪክ፣ የትግል አስተዋጽኦና የድርጅቱን ፖሊሲ በሜልበርን-አውስትራሊያ ለሚገኙ ኢትዮጵያውያን ገለጣ አድርጓል::

በዕለቱ የሕዝባዊ ውይይቱ አጀንዳ፣

1) የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲ ድርጅቶች አመሠራረት ታሪክ፣ የትግል አስተዋጽኦ እና
2) የፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲ የሚል ነበር::

መድረክ ኢትዮጵያ በአውስትራሊያ ለመጀመሪያ ጊዜ ባዘጋጀው በዚሁ ሕዝባዊ ስብሰባ ላይ ኢ.አአግን ጨምሮ የሃይማኖት ድርጅቶች፣ የሲቪክ ማኅበራትና የፖለቲካ ድርጅቶች የተጋበዙ ሲሆን የአፋር ኮሙዩኒቲ ማኅበርና የአካባቢው ኢ.ሕአፓ ተውካይ ተገኝተው የድርጅቶቻቸውን አመሠራረት ታሪክ፣ የትግል አስተዋጽኦና ፖሊሲዎቻቸውን አስተዋውቀዋል::

ኢ.አአግን ወክለው የድርጅታቸውን የተጋድሎ ታሪክና ፖሊሲ ያስተዋወቁት የኢ.አአግ የፖለቲካና የውጭ ግንኙነት ኃላፊ የሆኑት አቶ ቢቾክ ዋን ናቸው::

የንግግራቸውን ሙሉ ቃል እነሆ::

የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያን!

ውድ የመድረክ ኢትዮጵያ ሰብሳቢ

አገራችን  ኢትዮጵያ የብዙ ዓመታት ታሪክ ባለቤት ስለመሆኗ፤ ጥንታዊ የሃይማኖት መጻህፍት፣ ፈላስፋዎችና ፀሃፊዎች የሚመሰክሩላትና ስለገናናነቷ በስፋት የጻፉላት ጥንታዊት ሃገር ነች።

ኢትዮጵያ የአያሌ ብሔረሰቦችና የተለያዩ እምነት ቤቶች ምንጭ፣ የአኩሪ ባሕል፣ ቋንቋዎችና ታሪክ ባለቤት ከመሆኗም በላይ የዜጎቿ ብሔራዊ ማንነት ማረጋገጫ ምልክቶችም ናቸው። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ታሪክ እንደምንረዳው ከሰማንያ በላይ የሆኑ የኢትዮጵያ ብሔረሰቦችና ማኅበረሰቦች ከጥንት ጀምሮ በጋብቻ ተዋህደውና ተከባብረው መኖራቸው የጋራ ታሪካቸው መነሻ ነው።

በብሔረሰብ፣ በቋንቋ፣ በባሕል፣ በሃይማኖት ወዘተ. ይለያዩ የነበሩ ሕዝቦች በታሪክ ሂደት የአንድ ሃገር አንድ ሕዝብ መሆን የቻሉት ኢትዮጵያ ውስጥም ብቻ አለመሆኑን ከታሪክ እንረዳለን።

ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየው የኢትዮጵያ አንድነት መለያ ከባዕዳን ወራሪዎችና ከውስጥ ጠላቶች ጋርም በመዋጋት አጥንቱን ከስክሶና ክቡር ደሙን አፍሶሶ በምንም ሳይለይ በአንድ ሰንደቅ ዓላማ ስር አንድ የኢትዮጵያዊነት ሰነልቦና ይዞ የተጓዘበትን የአልበገሬነት የሃገር ፍቅር አርማው በወያኔ የዘረኛነት ፖሊሲ እየተሸረሸረ ይገኛል።

ኢሕአዴግ በነፍጥ ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የኢትዮጵያን ሕዝብ በክልልና በብሔረሰብ አለያይቶ በማደራጀት እርስ በርስ እንዲጋጩና እንዲጨፋጨፉ ማድረግ  ዋነኛ ተግባሩ መሆኑ እንግዳ አይደለም። ከ እዚህም አልፎ ራሱ ሰራዊት እያዘመተ የአንድነት ስሜት በሚያንጸባርቁ ሕዝቦች ላይ የዘር ማጥፋት ዘመቻ እያካሄደ ይገኛል። በደቡብ፣ በቤንሻንጉልና በጋንቤላ ክልሎች የተፈጸሙትና እየተፈጸሙ ያሉት ጭፍጨፋዎች ዋነኛ ማረጋገጫዎች ናቸው።

ያለመረጋጋት የጭንቀት ሕይወት እንዲገፋ የተገደደው የኢትዮጵያ ሕዝብ እጣው ችግርና ረሃብ፡ እርዛትና ስደት፣ ደዌና ሞት ሆኗል።

በአድሎአዊነት ላይ የተመሰረተው የወያኔ የ ኢኮኖሚ ፖሊሲ ለአንድ ክልል ብቻ ትኩረት በመስጠቱ የተቀረው የ ኢትዮጵያ ግዛት ክልል ሕዝብ ኑሮ ከለት ወደ እለት እየተሽመደመደ መሆኑ ግልጽ ነው። ከዚህም ሌላ ዋነኛው የእውነተኛ ዴሞክራሲያዊ ገጽታ የሆነው የዜጎች ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶችን የማስከበሩ ተግባር በወያኔ መንግሥት የቀን ሕልም ሆኗል፡፤

ይህንን ሁለገብ የአስተዳደር ጨቋኝነት እንዲያበቃ ለማድረግና የኢትዮጵያን ሕዝብ ከዚህ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ቀንበር ለማላቀቅ የኢትዮጵያ የቁርጥ ቀን ልጆች ለሕይወታቸው ሳይሳሱ በተገኘው መድረክና አጋጣሚ ሁሉ ከእነኚህ ኀጠኞች ጋር በሰላማዊ መድረክና የወቅቱ ትግል በሚጠይቀው መልክ ሁሉ የትግሉን ስልት መንደፍ ግድ ብሏል፡፤

ከዚህም አንጻር የኢትዮጵያ ሕዝብ ጩኸትና ለቅሶ ምላሽ ለመስጠት፤ ታግሎ ለማታገል፤ በአገር ውስጥና በውጭ የሚገኙ ኢትዮጵያውያንን ማሰባሰብና ለማታገል የሚችል ድርጅት ወቅቱ የሚጠይቀው የትግል ዘዴ ሆኗል።

ስለሆነም በወያኔ ላይ ሁለገብ ትግል ያስተባብር ዘንድ የኢትዮጵያ አንድነት አርበኞች ግንባር/ኢ.አ አግ እ.አ.አ. በ1994 ዓ.ም. ተመሰረተ።

ኢ.አአግ ከተለያዩ ብሔረሰቦች፣ ማኅበረሰቦች የተውጣጡ ከማንኛውም ሃይማኖታዊና መንፈሳዊ እምነቶች ተከታዮች ጋር የማይወግኑ “እምነት የግል ሃገር የጋራ” የሚል መርሆ የተቀበሉና ለአንድ አገር፣ ለአንድ ሕዝብ፣ ለአንድ ሰንደቅ ዓላማና በአንድ የጋራ ዕድል በሚያምኑ ጠንካራ አባላት ስብስብ የተመሰረተ ብሄራዊ ድርጅት ነው።

የተከበራችሁ ኢትዮጵያውያን!

ኢአአግ ብሔራዊ አጀንዳ ያለውና በኢትዮጵያ አንድነትና ልዑላዊነት እምነት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ አበይት አላማዎቹ በዚህ ዙሪያ የተመሰረቱ ናቸው።

1) በኢትዮጵያ ሕዝብ ጫንቃ ላይ በጉልበት የወጣው የወያኔ አገዛዝ እንዲወገድ በማድረግ የአገሪቱን ልዑዋላዊነትና ብሔራዊ ክብር ማስመለስ ፣
2) የዜጎች መብቶችና ነፃነቶችን ማረጋገጥና እውነተኛ ዴሞክራሲ በማስፈን ሥልጣን ለሕዝብ እንዲሆን ማድረግ፣
3) የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በነፃ ገበያ መርሆዎች ፖሊሲ ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ማድረግ ናቸው።

ኢአአግ ባሳለፋቸው የትግል ጊዜያት ዋነኛ ሆነው የገጠሙት ችግሮች ሌሎችንም ድርጅቶች ሳይገጥማቸው አይቀርም ብዩ ከምገምታቸው ውስጥ አንዱ የዓለም ፖለቲካ ሁኔታ መለዋወጥ ያስከተለው የፖለቲካ ተጽእኖ ነው። የቀዝቃዛው ጦርነት ማብቃትና በሽብርተኞች ላይ የታወጀው ጦርነት (war on terrorism) የወያኔ መንግሥትን ጀርባ በመጠኑም ቢሆን ያጠናከረ መሆኑ ከሁላችንም የተሰወረ አይደለም።

ከዚህም ሌላ እውነተኛ ትግል ላይ ያሉ ድርጅቶች ከኢትዮጵያውያን አስፈላጊ ሞራላዊና ቁሳዊ ድጋፍ እንዳያገኙ የተቃዋሚ ድርጅቶች መብዛትና አብሮ መሰለፍ አልመቻል ትልቁና ዋነኛው የወቅቱ ችግር ሆኗል።

ይህን ሁኔታ መፍትሄ ካላገኘ የተቃዋሚ ድርጅቶች እንቅስቃሴ የሚዳከም ከመሆኑም በላይ ተጠቃሚው የወያኔ መንግሥት መሆኑን መገንዘብ ያስፈልጋል። ስለሆነም ለነዚህ ችግሮች መፍትሔ ለመስጠትና በሚደረገው ትግል ወስጥ የግለሰቦችና የድርጅቶች ሚና እየጎለበተ እንዲሄድ ለማድረግ የሲቪክ ማኅበራት ሚና ልዩ ሥፍራ የሚሰጠው መሆኑን ኢአአግ አበክሮ ያምናል።

በዚህ አጋጣሚም ይህንን ጠቃሚ ሚና በመገንዘብና ለሃገራችን ኢትዮጵያ ያላቸውን ራዕይ ሕዝባዊ አጀንዳቸው አድርገው ይህ መድረክ እውን እንዲሆንና በዛሬው እለት የኢትዮጵያ ልጆች የሆን ሁሉ ተሰባስበን በአገራችን ጉዳይ ላይ ለመምከር እንድንችል ላደረጉት የመድረክ ኢትዮጵያ በአውስትራሊያ መሥራች አባላት ያለኝን ጥልቅና ልባዊ ምሥጋና በራሴና በኢአአግ ሰም ለማቅረብ እወዳለሁ።

ኢአአግ ያሸንፋል!
ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!

አመሰግናለሁ!